# የአይ.ሲ.ጂ ሪፖርት መሠረታዊ ስህተቶች

ከአሊ. አባዳማ

ዓለም አቀፉ የቀውስ አስወጋጅ ቡድን /አይ.ሲ.ጂ/ "ጎሣን መሠረት ያደረገ የፌደራላዊ መንግስት አወቃቀር በኢትዮጵያ እና ያስከተለው ስጋት" በሚል ርዕስ ኢትዮጵያን የሚመለከት አንድ ሪፖርት መሳይ የፕሮፖጋንዳ ጽሁፍ ሰሞኑን መልቀቁ ይታወሳል፡፡ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ የመንግስት መዋቅር ላይ ግልጽ ጥላቻ ከመያዝ ተነስቶ የተዘጋጀው ይህ ሪፖርት በርካታ ከባድ ስህተቶችን ይዞ ከመውጣቱ ባሻገር በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ጥላቻን ያንፀባረቀ፣ ሕሊናን የሚያውክ እና የሚያሳዝን ሪፖርት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በርግጥም የሪፖርቱ ርዕስ የጉዳዩን ምንነት ፍንትው አድርጎ ያሳየ ሲሆን በቀጣዩ ዓመት ለሚከሄደው የፌደራል እና የክልል ምርጫ ዝግጅቱ እየተጀመረ ባለበት በአሁኑ ወቅት የአንድ ወገን አቋምን ብቻ የሚያንፀባርቀው የዚህ ሰነድ ብቅ ማለት ለምን እንደሆነ በርካታ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ሆኗል፡፡ ይህንኑ ጥርጣሬ ይበልጥ የሚያጉላው ደግሞ መንግስት ለተቃዋሚዎች ሥልጣኑ ስለሚያጋራበት ሁኔታ እንዲያጠና ቡድኑ ከመጠየቅ አልፎ ዓለም አቀፉ ማነበረሰብ የምግብ ዋስትናን ለሚረጋገጥ ለኢትዮጵያ በሚያደርገው እገዛ ላይ ከማተኮር ይልቅ በመንግስት አስተዳደር ጉዳይ ላይ በማተኮር በመንግስት ላይ ጫና ሊያሳድርበት ይገባል ሲል ጥሪ ማቅረቡ ነው፡፡ ቡድኑ ያቀረበው ሪፖርት አሁን በኢትዮጵያ ካለው ተጨባጭ ዕውነታም ጋር ይሁን የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአገሪቱ እውን ለማድረግ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ ከነበረው ጥረት ጋር አንዳችም ተያያዥነት የሌለው ነው፡፡

ሪፖርቱ ጽሁፉን የሚጀምረው ኢትዮጵያ በፌደራላዊ መንግሥት አወቃቀር ያላትን ተሞክሮ በማጣጣል ሲሆን ይኸውም የአንድ ፓርቲ የበላይነት ከገነነበት ሥርዓት ጋር በማመሳሰል እና ቡድኑ ራሱ ከሚያምንበት ምናባዊው የሊበራል ዴሞክራሲ እና ነፃነት ጋር በማነፃፀር ነው፡፡

ሪፖርት የማጠናቀሩ ሥራ የተካሄደው ይህነው በሚባል የመስክ ጉብኝት ሳይሆን ይልቁንም አጫጭር የአዘቦት ቀናት ጉብኝት እና በአገሪቱ የምርጫ ሂደት ላይ የሚከመሰያ ጥናት በማካሄድ ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ በመሆኑም አመጣጡ ለኢትዮጵያ ጥላቻ ካላቸው የመረጃ ምንጮች / ይህንንም እንደእውነቱ ከሆነ ሪፖርቱ የሚደብቀው አይደለም/ አሊያም ለአንድ ወገን ብቻ ጥብቅና ከቆሙ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ አብዛኞቹ ኢንተርቪው የተደረገላቸው ሰዎች ከየት እንደመጡ ወይም በአገሪቱ ካሉት ብሔር ብሔረሰቦች ከየትኞቹ እንደሚመደቡ ለመገመት አዳጋች ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ፣ በብሔር ብሔረሰብ አሠፋፈር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀርን ለመተቸት ወሣኝ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ትክክለኛና ነፃ መረጃን መስጠት የሚችሉ አያሌ ምሁራን መኖራቸው እየታወቀ እነሱን ለማነጋገር ጥረት አለመደረጉ የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ ሪፖርቱ ጉዳዩን ካነሳ አይቀር ስንት ብሔር ብሔረሰቦችን በዝርዝር እና በጥልት ለማየት እንደ ሞከረ ማወቁም አግባብነት ያለው ጥያቄ ነው የሚሆነው፡፡ ከሪፖርቱ በመነሳት ይህንን ለማድረግ እንዳልተሞከረ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ በኢንተርቪው ወስጥ እንዲካተቱ የተደረጉ ሴቶችስ ነበሩን? እንዳልነበሩ ግልጽ ነው፡፡ የሪፖርቱ አጠናቃሪ/ዎች/ ከአዲስ አበባ ወጣ ብለው ዕውነታውን ለማየት ሞክረዋልን? ከሆነስ ወደት ነበር ወጣ ያሉት? ይህንንም በተመለከተ ሪፖርቱ አንድ ወይም ሁለት በሚሆኑ

ቦታዎች ካልሆነ በስተቀር ከአዲስ አበባ ውጭ ያለውን አመለካከት ለመቃረም አንዳች ጥረት ስለማይደረጉ ሪፖርቱ የሚሰጠው ፍንጭ አናሳ ነው፡፡ ለምሣሌ ስለኡብነግ የተጠቀሰውን አባሪ መረጃ ብንወስድ ከባድ ስህተቶች የታጩበት ከመሆኑም በላይ በሶማሌ ብሔራዊ ክልል  እየተካሄደ ስላለው የፖለቲካ ሽግግር ሂደት የሚታወቅ ነገር ስለመኖሩ ያልተንፀባረቀበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ሪፖርቱ ሌላው ቀርቶ በያንዳንዱ ቦታ ያለው የመንግስት እና የመንግሥታዊ አስተዳደር ማሻሻያ ሂደት ሁኔታ ከ1983 ጀምሮ ለውጥ ሳይደረግበት ባለበት ሁኔታ እንደቀጠለ ነው የሚል መልሻ ግምት ያስቀምጣል፡፡ ይህ ደግሞ አጠናቃሪው /ዎቹ/ የዛሬ 10 እና 12 ዓመታት በፊት የነበሩ ሰነዶችን እያጣቀሱ አሁን በአገሪቱ ያለውን አስተሳሰብ ለማሳያነት እንዲጠቀሙበት አስችሎአቸዋል፡፡ በዚያ ላይ ከ1984 እስከ 1997 ዓ.ም የነበሩትን ምርጫዎች ከላይ ከላይ ገረፍ በማድረግ ብቻ በያንዳንዱ ምርጫ መሃል የነበረውን ልዩነት ለማወቅ ጥረት ሳያደርጉ ሁሉንም በአንድነት በማየት ብቻ ባለፉት 18 ዓመታት ወስጥ በፖለቲካ የሽግግር ሂደት የተመዘገቡ ትላልቅ ለውጦችን ቢያንስ ቢያንስ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መፈጠሩን እንኳ ለማየት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ ሪፖርቱ ከ1983 ጀምሮ በአገሪቱ ሲካሄድ የኖረውን የለውጥ ሂደት መሉ በመሉ ትቶታል፡፡ በኢኮኖሚው እና በፖለቲካው መስክ ስለመተመዘገበት ማንም ሊክዳቸው ስለማይችላቸው ወጤቶችም የተባለ ነገር የለም፡፡ ዓለም አቀፉ የቀውስ አስወጋጅ ቡድን የተከተለው አቀራረብ የኤርትራው መንግሥት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊነትን እና የዴሞክራሲ ግንባታ ሥርዓትን አስመልክቶ ከሚከተለው አቀራረብ ጋር እጅግ የሚመሳሰል ሲሆን ይህም በአጋጣሚ የተከሰተ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡

የኤርትራው አመራር በአሁኑ ሰዓት ጠንክሮ እየሰራ ያለው የኢትዮጵያን መረጋጋት እና ዴሞክራሲን ለማጨናገፍ መሞከር ነው በባል ሚሆነን አይደለም፡፡ በዓለም አቀፉ የቀወስ አስወጋጅ ቡድን እና በኤርትራው አገዛዝ መካከል ያለው ብቸኛ ልዩነት ቡድኑ ዐመጽን ለመቀስቀስ እና መረጋጋትን ለማስቀረት ጥረት የማያደርገው ብዕሩን ተጠቅሞ መሆኑ ላይ ነው፡፡ የኤርትራው አመራር ከዚያ አልፎ ስለሚሄድ ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ይፋ ትብብር መኖሩን ማመት  የሚከብድም አይደለም፡፡

አጠናቃሪው /ዎቹ/ በሪፖርቱ ላይ ይህንንም ያንንም እያነሱ ሲዘባርቁ የተባለውን ጉዳይ ለማረጋገጥ ግን እንደተቸገሩ በተደጋጋሚ ሲገልፁ ይስተዋላሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ መንግሥት ሥልጣኑን ለማጋራት ወይም ትችትን ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆነ አድርገው ሲገልፁ እንኳ ማረጋገጫ አልሰጡም፡፡ በምርጫ ሥልጣን የያዘን መንግሥት መራጩሕዝብ በካርዱ ለጣለው ተቃዋሚ ፓርቲ ሥልጣን ያካፍል ብሎ ማለት በራሱ በአፍራሽነት የሚታይ ነው፡፡

የዓለም አቀፍ የቀወስ አስወጋጅ ቡድን ይህንን በመደበቅ ረገድ እንኳ ለምን ብልጥ ለመሆን እንዳልቻለ ያስገርማል፡፡ ምናልባትም ቡድኑ  በጠንካራ አቋሟቸው ኢትዮጵያን በመጥላት የሚታወቁትን  አንድ የቀደሞ የኤርትራ ባለሥልጣንን ከመሾም ጋር በተያያዘ ባሳየው ማንአለብኝነት ተደፋፍሮ ያደረገው ሊሆንም ይችላል፡፡ አሊያም ወደ ኋላ ላይ ለማዘራራት እንደሚሞክረው ከበስተጀርባው ካለ ሌላ ፖለቲካዊ ምክንያት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

ትችት አንድ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን የተሳሳተ፣ የመረጃ ጉድለት ያለበት፣ ወገናዊነት የሚንፀባረቅበት እና ያልተሟላ ትችት ትክክለኛ ሊሆን አይችልም፡፡ መንግሥት በሥልጣን ላይ በመቆየቱም ብቻ መተቸት አፍራሽ ነው፡፡ በ1997 ዓ.ም በተካሄደው የመድብለ ፓርቲ ምርጫ ላይ ኢህአዴግ አሸንፏል፡፡ ይህንን የዓለም አቀፉ የቀውስ አስወጋጅ ቡድን እንኳ ሊደብቀው የማይችለው ሐቅ ነው፡፡

ሪፖርቱ በ1997 እና ከዚያ ወዲህ ስላሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች በዝርዝር የሚያቀርብ ቢሆንም ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ የሚከተሏቸውን ፖሊሲዎች በተመለከተ ግን አንዳችም ነገር ከማንሳት ተቆጥቧል፡፡ ለምን? እነዚህን ፖሊሲዎች ለመለየት ይሞክር በባልም ያኔም ይሁን አሁን ቀላል እንዳልሆነ ቢታወቅም ሪፖርቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የተቃዋሚዎችን ምላሽ ጠይቆ ለማገኘት አሊያም ፖሊሲዎቻቸውን አፈላልጎ ለማገኘት ጥረት አለሚደረጉ ግምት ላይ ይጥለዋል፡፡ ቡድኑ ይህንን ያላደረገው በአብዛኛው የኢህአዴግን ፖሊሲዎች በመተቸት ላይ በሰፊው በማጠመዱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንደዕውነቱ ከሆነ ሪፖርቱ የተቃዋሚዎችን ፖሊሲዎች በይፋ ሲደግፍ የመንግሥትን ዓላማ እና ወጥን ሃሳቦቹን ሁሉ እስከ መጨረሻው ድረስ እንደተቃወመ የቀጠለበት ሁኔታ የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ በማስረጃ ላይ ተመስርቶም ይሁን ያለ ማስረጃ መንግሥት ለሚያወጣቸው ሕግጋት የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት በኩልም ተምሣሌት ሆኗል፡፡ ለአብነት ያህልም በቅርቡ የወጡትን የበጐ አድራጐትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አዋጅ፣ የፕሬስ ሕግ እና የፀረ - ሽብር ሕግን ለምን ማውጣት እንዳስፈለገ ለማወቅ ጥረት አላደረገም፡፡ እነዚህ ሁሉ ሕግጋት ግን በአውሮፓ አገሮች እና በአሜሪካ ካሉት ሕግጋት ጋር ከሞላ ጐደል ተመሣሣይነት ያላቸው ናቸው፡፡ እንግዲህ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ትችቶች ሁሉ ናቸው በአንድነት ታጭቀው በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ እየጠበበ ለመምጣቱ ማሳያ ሆነው በሪፖርቱ የተጠቀሱት፡፡ የሪፖርቱ አጠናቃሪ /ዎች/ ከእነዚህ ሕግጋት አንዳቸውንም በወጉ እንዳላነበቡ፣ እነሱን ከማውጣት በስተጀርባ ያለውን የመንግስት ፍላጐት ምንነት ለመገንዘብ እንዳልሞከሩ ግልጽ ነው፡፡

ሪፖርቱ ከዚህ አልፎ በመሄድ የሥልጣን መጋራት ሃሳብን ገፍቶበታል፡፡ ይህ ሃሳብ በ1997 ዓ.ም የተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ወጤት ከታወቀ በኋላ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማስቀጠል ረገድ አዚህ ግባ የሚባል አስተዋፅዖ ባላደረጉ ወገኖች እየቀረበ ያለ ሃሳብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሪፖርቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊነት ላይ አገኘሁት የሚለውን አንዳች ነቀፋ እያጎነ የመሄዱን ያህል ጠቃሚ የሆኑ የሚያጉሉ መረጃዎችን ደግሞ ሆን ብሎ እየደበቀ የመጣበት ሁኔታ አስገራሚ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሪፖርቱ በ2002 ዓ.ም በኢትዮጵያ በሚካሄደው ምርጫ ላይ ተጽዕኖ ለማሳረፍ እና የምርጫውን ወጤት ለማዛባት ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ሴራ አካል አይደለም ብሎ ለማመን የሚከብድ ይመስለኛል፡፡

ኢህአዴግ ከ1983 ጀምሮ በአገሪቱ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረጉን የዓለም አቀፉ የቀውስ አስወጋጅ ቡድን ሪፖርት አጠናቃሪ /ዎች/ ያመኑት ጉዳይ ቢሆንም ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች በምርጫ ኮሮጆ ወጤት ሥልጣን የመያዝ ሕጋዊ መብት አላቸው ብሎ እንደሚያምን እና በዚህም ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ዕውን መሆን በሙሉ ልቡ እየሰራ እንዳልሆነ አድርገው ማቅረባቸው እርስ በርሱ የሚቃረን ሃሳብ ነው፡፡ ሪፖርቱ ተቃዋሚዎች ከምርጫ 97 ወጤት በኋላ ራሳቸውን ከፖለቲካ ሂደቱ ማገለላቸውን እና እርምጃውንም የወሰዱት የምርጫውን

መጭበርበር በመቃወም ተደርጎ እንደሚታይ ጠቆም አደርጎ ሲያልፍ ማጉረምረምን የምርጫውን ወጤት ስለመቀበሉ ግን አለመግለፁም አሳፋሪ ነው፡፡

የሪፖርቱ አጠናቃሪ /ዎች/ በአብዛኛው የተማሙት ተቃዋሚዎች እና የማጉረምረም ነቃፊዎች በሰጠዋቸው መረጃዎች ላይ ሲሆን ከእነዚህ ምንጮች የሚበዙት በ1997ቱ ምርጫ የተሸነፉ፣ ያሸነፏቸውን የፓርላማ መቀመጫዎች ከመያዝ እና ያሸነፉትን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ከመረከብ አሻፈረን ብለው ለዴሞክራሲያዊው ሂደት ጀርባቸውን የሰጡ ናቸው፡፡ ይህ የፖለቲካ ፓርቲዎቹና አመራሮቹ እርምጃ በዴሞክራሲ ላይ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ደባ ነው ብለው የሚያምኑ በርካታ ፖለቲከኞች አብዛኞቹን የተቃዋሚ ፓርቲዎች እና አመራሮች መኖራቸውን ሪፖርቱ መጥቀስ በቻለ ነበር፡፡ አጠናቃሪው /ዎቹ/ ስለዴሞክራሲ ባወሩ ቁጥር የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን የሚያወዳድሩት የምርጫ ወጤት ምንም ይሁን ምን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ሥልጣን ከማሥራት ጋር ነው፡፡ ይህም ትልቅ ስህተት ወይም ቅጥፈት ነው፡፡

የዓለም አቀፍ የቀወስ አስወጋጅ ቡድኑ ባዘጋጀው ጽሁፍ ወስጥ ይህ የተሳሳተ አቀራረብ መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ጽሁፉ በአገሪቱ ጥሩ ጥሩ ለወጦች መካሄዳቸውን ለማመን በሚገደድበት ጊዜ እንኳ ከለወጦቹ ጀርባ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው መኖሩን በምክንያትነት ለመጥቀስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በአገሪቱ ልዩ ልዩ የፖለቲካ አመለካከቶች በመስተናገድ ላይ መሆናቸውን እና የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መፈጠር መቻላቸውን ለማለጽ ሲገደደም ወዲያውኑ በሚያያዝ የሚያቀርበው ሌላ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በአገሪቱ ካለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጋር ተያያዥነት እንደሌለው፣ ይልቁንም "በብሔራዊ ደረጃ ያለው የፖለቲካ አመለካከት ወደ ሁለት ጽንፎች በማምራቱ የተነሳ የተፈጠረ" እንደሆነና ይህም በፓርቲዎች ወስጥ እና በፓርቲዎች መካከል ወጥረትን እያባባሰ እንዲመጣ ያደረገ መሆኑን አክሎ ይገልፃል፡፡ ይህ በራሱ ከኤርትራ በኩል ዘወትር ከምንሰማው መከራከሪያ ነጥብ ጋር እንዲገጥም ለማድረግ ታስቦ እወነታውን ምን ያህል የማጠምዘዝ ሥራ እንደተካሄደ የሚጠቁም ምሣሌ ነው፡፡

ይህም በመሆኑ አይ ሲ ጂ ያቀረበው ሪፖርት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም ሪፖርቱ በወስጡ አንድም እወነታን ያልያዘና ከተራ አሉባልታ ተለይቶ የሚታይ ባለመሆኑ፤ አገራችን የጀመረችውን የልማቱና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚያመጣው አንዳችም ተጽእኖ አይኖረውም፡፡ ሰላም!